| **የፖሊሲ ርእስ፡** የገንዘብ እርዳታ ፖሊሲ | **የእትም ቁጥር፡** 6 |
|---|---|
| **ቃላትን መፈለግ፡** | |
| **ኦርጂናል ፖሊሲ ቀን፡** 12/31/15 | **የተከለሰበት ቀን፡** 5/1/2018፣ 5/1/2019፣ 05/29/2020፣ 5/28/2021፣9/30/2021 |
| **ከታች በፈረመው ሰው የፀደቀ፡**<br><br>______________________________________<br>Alice Pope, CFO | |

## I. ዓላማ

የInova ዓላማ ለምናገለግለው በማንኛውም ማሕበረሰብ ውስጥ ላለው ማንኛው ሰው፣ ሁሉ ግዜ ደረጃውን የጠበቀ የጤና እንክብካቤ ማቅረብ ነው፡፡ ከታክስ ነፃ የሆነ የቴና አገልግሎት ድርጅት እንደመሆኑን እና በዓላማውም መሠረት፣ Inova የድንገተኛ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ሕክምናዎችን፣ የመክፈል አቅማቸውን ከግምት ሳያስገባ ያቀርባል፡፡

## II. ፖሊሲ

Inova ይህን የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ *(Financial Assistance Policy (FAP))* ያዘጋጀው፣ ሃብቱን በኃላፊነት ለመጠቀም እና Inova በተቻለ መጠን ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ የሚገባውን ድጋፍ ማቅረብ እንዲያስችለው ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ይህ ፖሊሲ የተቀረፀው፣ የሃገር ውስጥ ገቢ ኮድ ክፍል 501(r)ን ጨምሮ፣ ማናቸውም አካባቢያዊ መንግስታት ገዥ ስምምነቶች እና ከሁሉም ተፈፃሚነት ያላቸው የስቴት እና ፌዴራል ሕጎች እና ደንቦች፡፡

በዚህ ፖሊሲ መሰረት፣ የገንዘብ ድጋፉ የሚሰጠው፣ በእያንዳንዳቸው የ Inova ሆስፒታል ተቋሞች እና ሌሎች በፖሊሲው የሚሸፈኑ ተቋማት እና አቅራቢዎች ድንገተኛ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የሕክምና አገልግሎቶችን ለሚጠቀሙ እና መስፈርቱን ለሚያሟሉ ግለሰቦች ነው፡፡

ፖሊሲው የሚያጠቃልለው፡

- በዚህ ፖሊሲ ውስጥ የተጠቀሱ የቃላት ፍቺዎችን፤
- ስለሚከተሉት የተሰጡ ማብራሪያዎችን፡
  - o በዚህ ፖሊሲ ለተሸፈኑ አገልግሎቶች የሚሰጡ የገንዘብ ድጋፎች፣
  - o እያንዳንዱን የገንዘብ ድጋፍ አይነት/ደረጃ ለማግኘት አንድ ግለሰብ ሊያሟላቸው የሚገቡ መስፈርቶች፣
  - o ግለሰቦች የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ማመልከት የሚችሉት እንዴት እንደሆነ፣
  - o Inova የገንዘብ ድጋፍ የሚፈልጉ ግለሰቦች ከሚያቀርቧቸው መረጃዎች ውጭ ብቁነትን ለማረጋገጥ ሊጠቀምባቸው የሚችላቸው የመረጃ ምንጮች፣
  - o ክፍያ ባልተከፈለበት ግዜ Inova ሊወስዳቸው የሚችለው እርምጃ፣
  - o Inova፣ ፖሊሲውን እንዴት አድርጎ በፖሊሲው በተሸፈኑ ሆስፒታሎች እና ተቋማት አገልግሎት የሚሰጠው ማኅበረሰብ ውስጥ እንዴት በስፋት እንደሚያስተዋውቅ፣

- o Inova እንዴት በአጠቃላይ የሚከፈለው መጠን *(Amounts Generally Billed (AGB))* ይወስናል እንዲሁም
- o በዚህ ፖሊሲ መሰረት ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ የሆኑ ታካሚዎች የሚከፍሉት የክፍያ መጠን የሚሰላበትን መነሻ፡፡

ለዚህ ፖሊሲ ሶስት አባሪዎች አሉት፡

- አባሪ A ተፈፃሚነት ያለውን የፌዴራል የድህነት መለያ መመሪያ ያቀርባል
- አፔንዲክስ B የትኛው የInova ማሳለጫና አቅራቢዎች በዚህ ፖሊሲ ሽፋን እንዳላቸውና እንደሌላቸው ይገልፃል
- አባሪ C ለገቢ እና መኖርያ መሰደን ተቀባይነት ያላቸው አጠቃላይ ዝርዝር ይገልጻል፡፡

ማንኛውም በዚህ ፖሊሲ ሽፋን የሚሰጣቸው የ Inova ሆስፒታሎች፣ አካላት ወይም አቅራቢዎች ብቁ ከሆኑበት አጠቃላይ የሚከፈለው መጠን ፋይናንሳዊ ድጋፍ በላይ ለሚጠቀሙ ግለሰቦች የሚያስከፍሉ ይሆናል፡፡

**አስተዳደር**
ይህ ፖሊሲ፣ ለሚመለከታቸው ትቋማት እና አካላት፣ ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት ፀድቋል፡፡

## III. ፍችዎች

ለዚህ ፖሊሲ አላማ፣ ከዚህ በታች ያሉት ቃላት እንደሚከተለው ፍች ተሰጧቸዋል፡

- **በአጠቃላይ የሚጠየቅ ክፍያ *(Amounts Generally Billed (AGB))*፡** ከ501(r) በታች፣ ሆስፒታሉ የሆስፒታሉን አጠቃላይ የህክምና ክፍያ በአንድ ወይ አጠቃላይ ክፍያውን (AGB ፐርሰንቴጅ)ከዛ በላይ በሆነ ፐርሰንቴጅ በማካፈል AGB ሊወስን ይችላል፡፡ የሆስፒታሉ ቢያንስ በዓመት የተሰጠውን የድንገተኛ ህክምና እና ለሌሎች አስፈላጊ ህክምናዎች ድምር ለነዚህ ህክምናዎች የሚገባውን ክፍያ በማካፈል AGB ፐርሰንቴጅ ማስላት ይኖርበታል፡፡ ስለ Inova የ AGB ስሌት የበለጠ መረጃ ለማግኘት የዚህን ፖሊሲ ገፅ 10 ይመልከቱ፡፡ ስለ AGB እና/ወይም ስሌት (ከክፍያ ነፃ ለሆኑ አገልግሎቶች) የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎትን በ571-423-5880 የInova ፋይናንሳዊ ድጋፍ ክፍል ያግኙ፡፡

- **የሚሸፈኑ አካላት፡** Inova አስቸኳይ እና/እንዲሁም ወይም ሌላ አስፈላጊ የህክምና እንክብካቤ የሚሰጥ ሲሆን የፋይናንስ ድጋፍ ፖሊሲ ተፈጻሚነት የሚያካትተው፡
  - o Inova የሆስፒታል ተቋማት፡
    - Inova Alexandria Hospital
    - Inova Fair Oaks Hospital
    - Inova Fairfax Medical Campus
    - Inova Loudoun Hospital
    - Inova Mount Vernon Hospital
    - Inova Loudoun Ambulatory Surgery Center
    - Inova Ambulatory Surgery Center at Lorton
    - Inova McLean Ambulatory Surgery Center
    - Inova Northern Virginia Surgery Center
    - Inova Franconia-Springfield Surgery Center
  - o ሌሎች ተዘዋዋሪ የ Inova ማሳለጫዎች፡
    - Inova Cares Clinic for Children
    - Inova Cares Clinic for Women
    - Inova Cares Clinic for Families

        - Inova Emergency Care Centers
    - የተመረጡ የ Inova የህክምና ቡድን የህክምና አገልግሎቶች (አፔንዲክስ B ይመለለቱ)

- **የተሸፈኑ አቅራቢዎች፡** ይህ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው የ Inova-ደጋፊ ሐኪሞች እና ሌሎች አቅራቢዎች፡፡ የተሸፈኑ አቅራቢዎችን ሙሉ ዝርዝር ለማየት አባሪ ለ B ይመልከቱ፡፡

- **የተፈቀዱ አገግሎቶች፡** በInova በሚሸፈኑ ነገሮች እና በሚሸፈኑ አቅራቢዎች ለፋይናንስ ድጋፍ ብቁ ሆነው የሚሰጡ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡ (1) በየአደጋ ጊዜ ሁኔታ በድንገተኛ ሕክምና መስጫ ክፍል ውስጥ የሚሰጥ የድንገተኛ ሕክምና አገልግሎት፤ (2) ለሂወት አስጊ በሆኑ ሁኔታዎች ከድንገተኛ ህክምና ክፍል ውጪ የሚሰጡ አገልግሎቶች፤ እንዲሁም (3) ሌሎች ለጤና አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶች፡፡

- **ድንገተኛ የጤና እክሎች፡** የሜዲኬር ተሳታፊ ሆስፒታሎች በማህበራዊ ድህነት ውል ክፍል 1867 (42 U.S.C. 1395dd) የተቀመጡ የአስቸኳይ የህክምና እንክብካቤ እና ሰራተኛ *(Emergency Medical Treatment and Labor Act) (EMTALA))* መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው፡፡ ድንገተኛ ህክምና ለሚያስፈልጋቸው ታካሚዎች ታካሚው ያለው ፋይናንሳዊ ድጋፍ ሁኔታ፣ የተረጋገጠ ሁኔታ፣ የመክፈል አቅም፣ የአሁን ወይ የከዚህ ቀደም የመሰብሰብ ሁኔታ ወይ ባለው ብደር ግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ ፖሊሲ መሰረት እኚህን የመሳሰሉ አገልግሎቶች አለመሰጠት የሚያበረታታ አይኖርበትም፡፡

- **ቤተሰብ፡** በውስጣዊ ገቢ መሰብሰብ አገልግሎት ሕግ መሰረት ታካሚው በግብራቸው ላይ ተጠጊ የሆነ ሰው እንዳለ ከተናገሩ ፋይናንሳዊ ድጋፍ ለማቅረብ እነዚህ ሰዎች እንደ ቤተሰብ አባል ይቆጠራሉ፡፡ Inova ለውሳኔው ተመሳሳይ መመርያዎችን ይከተላል፡፡ የገቢ ማረጋገጫ በማምልከቻው በድጋፍ ከተዘረዘሩ አስፈላጊ ከሆነ ይጠይቃል፡፡

- **የቤተሰብ ገቢ፡** የቤተሰብ ገቢ የሚወሰነው እንደሚከተለው ነው፡
    - ከቢው ከታክስ በፊት ባለው መሰረት ይሰላል፤
    - የሚያጠቃልለው፤ የሥራ ገቢ፣ የሥራ አጥነት ክፍያ፣ የሰራተኛ ክፍያ፣ የማኅበራዊ ደህንነት፣ ድጋፍ ሰጪ የደህንነት ገቢ፣ የሕዝብ ድጋፍ፣ የአባት ጦር ክፍያዎች፣ የከአደጋ ተራፊዎች ጥቅማጥቅሞች፣ የጡረታ ገቢ፣ ወለድ፣ የትርፍ ክፍያ፣ የኪራይ ገቢ፣ የአዕምሮአዊ ንብረት ክፍያ፣ የቤት ባሌቤትነት ገቢ፣ እርዳታዎች፣ የትምህርት ድጋፍ፣ የተቆራጭ ገቢ፣ የልጆች ድጋፍ ገቢ፣ ከቤት ውች የሚገን ድጋፍ፣ እና ሌሎችም ምንጮች፤
    - የካፒታል ኪሳራዎች አይካተቱም፤ እንዲሁም
    - የ IRS መመርያዎች በመከተል የቤተሰብ አባል ታካሚው የገቢ ግብር እንዲመለስለት ከጠየቀ የቤተ ሰብ አባላት ግምት ውስጥ ይገባሉ እንዲሁም የቤተሰብ አባላቱ ገቢ መካተት አለበት፡፡

  አጠቃላይ ተቀባይነት ያለው ዝርዝር ሰነድ በአባሪ C ውስጥ ይገኛል፡፡

- **FAP-ብቁ የሆነ ግለሰብ፡** በዚህ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ መሰረት፣ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ መሆኑ በ Inova የተመሰከረለት ግለሰብ፡፡

- ***የፌዴራል ድህነት መለያ መመሪያ (Federal Poverty Guidelines (FPG))*፡** የድህነት መመርያዎች በአሜሪካ የጤናና የሰዎች አገልግሎት ምዘገባ ክፍል በየግዜው የሚሻሻል ነው (አፔንዲክስ A ይመልከቱ)፡፡

- **የገንዘብ ድጋፍ፡** የገንዘብ ድጋፍ የሚያጠቃልለው፣ የ Inova ን የገንዘብ ድጋፍ መስፈርቶች ለሚያሟሉ እና ለሚያስፈልጋቸው አገልግሎት በሙሉ ወይም በከፊል መክፈል ለማይችሉ ሰዎች የሚሰጡ ቅናሽ የተደረገባቸው ወይም ነፃ የጤና አገልግሎቶችን ነው፡፡ የገንዘብ ድጋፍ የሚከተሉትን አያካትትም፡ የተበላሹ ብድሮች ወይም Inova እንደገቢ የመዘገባቸው፣ በኋላ ግን ታካሚዎች ባለመክፈላቸው እንደ ፍጆታ የመዘገባቸው መሰብሰብ የማይችሉ ክፍያዎችን፣ በሜዲኬድ ወይም ሌላ ምንጭ-ፍቱን ከሆነ የመንግስት ፕሮግራሞች ሥር የተሰጠ የሕክምና ወጪ እና

ከእነሱ በተገኘው ገቢ መካከል ያለ ልዩነት፤ ራስ በመክፈል ወይም ቶሎ በመክፈል የሚገኙ ቅናሾች፣ ወይም ከማንኛውም ሶስተኛ ወገን ከፋይ ጋር የተፈፀሙ የውል ስምምነቶች፡፡

- **ጠቅላላ ክፍያዎች፡** ለታካሚው ለሚሰጡ አገልግሎቶች ድርጅቱ የሚያስከፍለው አጠቃላይ መደበኛ ክፍያ፣ ከገቢ የሚቀነሱ ተቀናሾች ሳይታሰቡ፡፡

- **የገቢ ማሳያ ሰነዶች፡** ተቀባይነት ያለው የቤተሰብ ገቢ ማሳያ ሰነድ፣ ቢያንስ ከሚከተሉት አንዱንን (1) መያዝ አለበት፡
  - o የመጨረሻውን የግብር መግለጫ ቅጅ፤
  - o የመጨረሻዎቹን 2 የደመወዝ መቀበያ ቲኬቶች፤
  - o እንደ የቤት ሊዝ ወይም የሸያጭ ሽግመልከቻ፣ የአውቶሞቢል ሊዝ ወይም የብድር ማመልከቻ ወይም ሌላ የገቢ ማረጋገጫ የሚያስፈልገው የሶስተኛ ወገን ሌላ አንድ የገቢ ማረጋገጫ በ Inova ተቀባይነት ያለው ተደርጎ ይወሰደል፡፡

አጠቃላይ ተቀባይነት ያለው ዝርዝር ሰነድ በአባሪ C ውስጥ ይገኛል፡፡

- **ለጤና አስፈላጊ የሆነ፡** በተገቢው መልኩ ህክምና ከተደረገ በታካሚው ጤና ላይ ለውጥ ሊያመጣ እሚችል ከሆነ ለእንደዚህ የመሳሰሉ ሁኔታዎች አገልግሎት፡፡ ባርያትሪክ አገልግሎቶች፣ የኮስሞቲክስ ህክምናዎችና እንዚህን የመሳሰሉ ሌሎች አገልግሎቶች በዚህ ፋይናንሳዊ ድጋፍ ፖሊሲ ሽፋን አይሰጣቸውም፡፡

- **Inova የአገልግሎት ቀጠና፡** የዚህ ፖሊሲ ሽፋን ዓላማ ሲባል፣ የ Inova አገልግሎት የሚዳረስበት ጂኦግራፊያዊ ክልል ቨርጂንያን ያካትታል፡፡

- **መድህን የሌለው፡** ታካሚው የክፍያ ግዴታውን እንዲወጣ የሚያግዘው ምንም አይነት የመድህን ሽፋን ወይም የሶስተኛ ወገን ድጋፍ የለውም፡፡

- **በቂ የመድህን ሽፋን የሌለው፡** ታካሚው የተወሰነ የመድህን ሽፋን ወይም የሶስተኛ ወገን ድጋፍ አለው፣ ነገር ግን አሁንም ከኪሱ ለመክፈል ከአቅም በላይ የሆኑ ወቺዎች አሉበት፡፡

## IV. ብቁነት

**የብቁነት መስፈርት እና የገንዘብ ድጋፍ አለ**

Inova ለግለሰቦች የገንዘብ ድጋፍ የሚያቀርበው በቤት ውስጥ የገቢ ሁኔታ፣ ባለው ንብረት፣ እና በመንግስት ለሚደገፉ ወይም ለሚደጎሙ የጤና መድህን ፕሮግራሞች ባለው ብቁነት ላይ በመመስረት ነው፡፡ በ Inova ሆስፒታል ተቋም፣ ሽፋን ያላቸው አካላት ወይ ሽፋን ያላቸው አቅራቢዎች ለሚቀርቡት አገልግሎት ብቁ ለሆኑና ዋስትና ለሌላቸው ፋይናንሳዊ ድጋፍ ለመስጠት ከታች በተጠቀሱት መለኪያዎች የሚወሰን ይሆናል፡፡

**1. የድንገተኛ ህክምና ወይ ድንገተኛ ላልሆኑ ነገር ግን አስፈላጊ ለሆኑ የህክምና አገልግሎቶች ፋይናንሳዊ ድጋፍ፡፡**
የInova ፋይናንሳዊ ድጋፍ መርሀግብር ለድንገተኛና ድንገተኛ ላልሆኑ ህክምና መክፈል ለማይችሉ ሰዎች እንደ መጨረሻ አማራጭ ታስቦ የቀረበ ነው፡፡ እነዚህ የመሳሰሉ ፋይናንሳዊ ድጋፍ ማመልከቻዎች የጉዞ ጤና መርሀግብር ወይ በሌሎች ሀገራት መንግስታት ወይ ዓለማቀፍ ድርጅቶች የግለሰብ አቅርቦት የመሳሰሉ የድርጅታዊ መርሀግብር ህክምናዎች ጨምሮ ተመሳሳይ ከሆኑ አካባቢያዊ፣ የስቴት ወይ የፌደራል መርሀግብሮች ጋር እንዲመሳሰሉ ይጠበቃል፡፡

A. **የአኗኗር ሁኔታ መስፈርቶች፡** በ ቨርጅንያ የሚኖር ግለ ሰብ እንዲሁም ብቁ አገልግሎት ካገኘ ለሰላሰ (30) ቀናት ወይም ከዛ የሚረዝም ጊዜ የኖረ ለአስቸኳይ የህክምና ሁኔታ ወይም አስቸኳይ ላልሆነ አስፈላጊ የክምና

አገልግሎት የሚውል የገንዘብ ድጋፍ ይደረጋል፡፡ የመኖርያ መስፈርቶች ለ Inova የሴቶች፣ ህጻናት እና ቤተሰብ እንክብካቤ ተግባራዊ አይደረግም፡፡

ግለ ሰቦች የአሁኑን አድራሻ በማካተት ከታች የተጠቀሱትን አንድ (1) ነገሮች በማሳየት በ ቨርጅንያ ነዋሪ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይችላሉ፡

- የቨርጅንያ መንጃ ፈቃድ ወይም በስቴት-የተሰጠ መታወቅያ
- ወርሀዊ የባንክ ሒሳብ ስቴትመንት፡፡ ከአገልግሎቱ በፊት በባንክ 30 ቀናት ወይም ከዛ በላይ የተሰጠ መሆን አለበት፤
- ወቅታዊው የአውቶሞቢል ወይ የሂወት ዋስትና ክፍያ፤
- ከአሜሪካ ውስጣዊ የግብር ስብሰባ አገልግሎት *(Internal Revenue Service (IRS))* የግብር W-2 ቅፅ ወይ 1099 ቅፅ ከ18 ወር ያልበለጠ ሪፖርት፤
- ካለፈው ዓመት የአሜሪካ ወይ ቨርጂንያ የተከፈለ የገቢ ግብር፤
- ለአመልካቾች የሚሰጥ የመገልገያ ቢል፡፡ ለምሳሌ ነዳጅ፣ ኤሌትሪክ፣ የቆሻሻ መድፍያ፣ የኬብል ወይ የስልክ ክፍያ ቢሎች ያካትታል፤
- የሊዝ ውል፤
- በአካባብያዊ ምዝገባ ለአመልካቹ የተላከ የቨርጂንያ የድምፅ ሰጪዎች ምዝገባ ካርድ፤
- ባለፈው ዓመት ውስጥ በኮመንዌልዝ ቨርጂንያ ወይ በቨርጂንያ አካባቢ ለግላዊ ንብረት ግብር ወይ የእሴት ታክስ ደረሰኝ፤
- የቨርጂንያ ትምህርት ክፍል ምዝገባ ቅፅ ሰርተፍኬት፤ እና/ወይም
- በአሜሪካ ግዛት ወይ ድንበር ውስጥ ተቀባይነት ያለው የትምህርት ቤት መረጃዎች/ትራንስክሪፕቶች ቅጂ፡፡
- ፊርማ ያረፈበት ደብዳቤ

አጠቃላይ ተቀባይነት ያለው ዝርዝር ሰነድ በአባሪ C ውስጥ ይገኛል፡፡

**B.** ከላይ የተጠቀሰውን የኗሪነት ቅድመ ሁኔታና ከታች የተጠቀሰውን የገቢ ቅድመ ሁኔታ ለሚያሟላ ግለሰብ ሶስት ዓይነት ፋይናንሳዊ ድጋፎች አሉ፡፡

1. **ዋስትና የሌላቸው ግለሰቦች፡** ዋስትና ለሌላቸውና የቤተሰባቸው ገቢ ከፌደራል የድህነት መመርያ *(Federal Poverty Guidelines (FPG))* 400% ወይም በታች ገቢ ላላቸው ታካሚዎች 100% የፋይናንሳዊ ድጋፍ ቅናሽ (ነፃ ህክምና)፡፡
2. **በቂ የመድህን ሽፋን የሌላቸው ግለሰቦች፡** በተጨማሪም 100% ፋይናንሳዊ ድጋፍ ቅናሽ (ነፃ ህክምና) ሽፋን ላላቸውና በ FPG መሰረት የቤተሰባቸው ገቢ 400% እና ከዛ በታች የሆነና (ለምሳሌ ሽፋን ለሌላቸው ግለሰቦችና ህክምና ካገኙ በኋላ ክፍያ እንዲከፍሉ የሚገደዱ) በከፊል ሽፋን ላላቸውና በዚህ ፖሊሲ በተገለፀው መሰረት ብቁ የሆኑና ዋስትናቸው ከዋስትና በኋላ Inova ፋይናንሳዊ ድጋፍ ቅናሽ እንዲያደርግ ሲፈቅዱ ነው፡፡ Inova እንደ አቅራቢ በማይሳተፍበት ኢንሹራንስ ስር ያሉ ታካሚዎች የInova ቅናሽ ወይ የጋራ ኢንሹራንስና ሌሎች የታካሚ ሀላፊነት ሊጋራ አይችልም፡፡
3. **የከፍተኛ አደጋ የገንዘብ ድጋፍ፡** ከላይ በተጠቀሰው ቅድመ ሁኔታ መሰረት ለነፃ ህክምና ብቁ ያልሆኑ፣ በተፈጥሯዊና በሚቀርበው አገልግሎት ምክንያት፣ በመኖርያ ቤትና ከሌሎች ሊኖሩ ከሚችሉ ምንጮች በተያያዘ ከፍተኛ የሆነ ፋይናንሳዊ ሀላፊነት ያላቸው ታካሚዎች የአደጋ ግዜ ፋይናንሳዊ ድጋፍ ቀርቧል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች የታካሚው ሀላፊነት ከቤተሰቡ ገቢ ወይ ከአጠቃላይ የሚከፈለው ክፍያ ከ15% በታች የሚገደብ ይሆናል፡፡

## 2. ቀድመው የሚወሰኑ ክፍያዎች፡፡

ቀደም ብለው የሚወሰኑ ቅናሾችን የሚቀበሉ ታካሚዎች (የፓኬጅ ዋጋ) ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ አይደሉም፡፡

**3. ልዩነትአለማድረግ፡፡**
የፋይናንስ ድጋፉ በገንዘብ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ሲሆን ዕድሜ፣ ስርዓ ጾታ፣ ጾታ፣ ዘር፣ የሀገር መነሻ፣ ማህበራዊ ወይም የስደተኛ ሁኔታ፣ የጾታ ምርጫ ወይም ኃይማኖት ግምት ውስጥ አያስገባም፡፡ Inova ከዚህም በተጨማሪ፣ የለገንዘብ ድጋፍ ብቁ መሆናቸውን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ፣ ያለ ልዩነት፣ ለድንገተኛ የጤና እክሎች ሕክምና ይሰጣል፡፡

**4. መንግስት ስፖንሰር ለሚያደርጋቸው ወይ ለሚደጉማቸው ኢንሹራንስ ወይ የግል ኢንሹራንሶች ለማመልከት ቅድመ ሁኔታዎች፡፡**
የ Inova የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራም የመድህን ፖሊሲ አይደለም፡፡ Inova ዋስትና የሌላቸው ታካሚዎች የጉዞ ጤና መርሀግብር ወይ በሌሎች ሀገራት መንግስታት ወይ ዓለማቀፍ ድርጅቶች የግለሰብ አቅርቦት የመሳሰሉ የድርጅታዊ መርሀግብር ህክምናዎች ጨምሮ ሌሎች በመንግስት ወይ የውጭ ድርጅቶች በሚደገፉ የጤና ዋስትናዎች ዓይነቶች የመሳሰሉ መንግስት ስፖንሰር በሚያደርጋቸው (ለምሰሌ ሜዲኬድ) ወይ መንግስት በሚደጉማቸው መርሀግብሮች/እቅዶች ላይ እንዲያመለክቱ Inova ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጣል፡፡ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት፣ አጠቃላይ ግላዊ ጤናና ንብረታቸውን ለመጠበቅ መንግስት ስፖንሰር በሚያደርጋቸው ወይ ሰራተኞችን መሰረት ያደረገ እቅድ የማግኘት እድል ያላቸው ታካሚዎች ነዚህ ላይ ማመልከት አለባቸው፡፡

**5. ተብሎ የሚታሰበው ፋይናንሳዊ ድጋፍ፡፡**

A. Inova ሁሉም ታካሚ ወይ የታካሚው ዋስ ፋይናንሳዊ ድጋፍ ማመልከቻ ሊሞላ እንደማይችል ወይ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች ላያቀርብ እንደሚችል ይገነዘባል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ፣ Inova ታካሚው ለፋይናንሳዊ ድጋፍ ብቁ ነው ብሎ በማሳብ የታካሚውን ወይ የታካሚው ዋስ ለፋይናንሳዊ ድጋፍ ብቁ መሆኑን የሚገልፀውን መረጃ ለመገምገም የሶስተኛ ወገን መረጃ ሊጠቀም ይችላል፡፡
B. ሒሳቡ በፋይናንሳዊ እንክብካቤ ሂደት ስር ብቁ ነው ተብሎ ከታሰበ ታካሚው ሒሳብ 100% ፋይናንሳዊ ድጋፍ ቅናሽ ያገኛል፡፡
C. በሚከተሉት ሁነቶች ወይ የተፈተኑ መርሀግብሮች ካመላከቱ Inova ግለሰቡ ብቁ እንደሆነ ሊያስብ ይችላል፡
    1. የቤት እጦት፤
    2. ያለ ምንም እሴት ሞት፤
    3. ተጨማሪ የምገባ ድጋፍ መርሀግብር *(Supplemental Nutrition Assistance Program (SNAP))*፤
    4. ለድንገተኛ ሜዲኬድ ብቁ የሆኑ ታካሚዎች በሜዲክኤድ የማይሸፈኑ ከድንገተኛ ወይ ድንገተኛ ያልሆኑ ነገር ግን አስፈላጊ የህክምና አገልግሎቶች ጋር ተያይዘው ለሚመጡ ድጋፎች ብቁ ይሆናሉ፤
    5. ለአካባብያዊ ወረዳ ችግረኞች ፕሮግራም ብቁ የሆኑ ታካሚዎች እንደዚህ በመሳሰሉ ሽፋን ለማይሰጣቸው ከድንገተኛና ድንገተኛ ያልሆኑ ነገር ግን አስፈላጊ ህክምና አገልግሎቶች ጋር ለተያያዙ ድጋፎች ብቁ ይሆናሉ፡፡

**6. በዚህ ፖሊሲ የሚጠበቅ**
የገቢ ዑደት ምክትል ፕሬዚደንት፣ የህዘብ ጤና ምክትል ፕሪዘደንት ፣ እንዲሁም የ Inova እያንዳንዱ የፋኩልቲ የፋይናንስ ምክትል ፕረዚዳንቶች ጉዳዩን በመከታተል የፋይናንስ ድጋፍ የመስጠት ስልጣን ያላቸው ሲሆን ይህ ካልሆነ በዚህ ፖሊሲ ስር ፋይናንሳዊ ድጋፍ ማግኘት አይቻልም፡፡

**7. ብቁ ነት፣ ግለሰቡ ከመንግስት ሽፋን ካላገኘ፡፡**
በመንግስት ለሚታገዝ ወይም በመግንስት ለሚደጎም የጤና መድህን ላመለከቱ፣ ነገር ግን በገቢ ወይም ሀብት ከፍተኛነት ምክንያት እና/ወይምየመድህን ፕሮግራሞቹ የሚጠይቁትን የአስቸኳይነት/የአካል ጉዳተኝነት መስፈርት ባለማሟላታቸው ምክንያት ተቀባይነት ላላገኙ ባለ ዝቅተኛ ገቢ ታካሚዎች የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

**8. የታካሚ የይግባን መብት፡፡**
አንድ ታካሚ በ Inova የገንዘብ ድጋፍ ብቁነት ውሳኔ ካልተስማማ፣ ታካሚው ውሳኔው በተሰጠ በ45 ቀናት ውስጥ የይግባኝ ማመልከቻ በፅሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡ የ Inova የገንዘብ ድጋፍ ቢሮ ማመልከቻውን ይመለከታል ከዚያም በ60 ቀናት ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## V. የማመልከቻ ሂደት

**ለገንዘብ ድጋፍ ማመልከት የሚቻለው እንዴት ነው?**

Inova የገንዘብ ድጋፍ የሚፈቅደው፣ የገንዘብ ድጋፍ ለመጠየቅ ጠንቅቆ በተሞላ ቅፅ (ማመልከቻው) መሰረት ነው፡፡ ስለ Inova ፋይናንሳዊ ድጋፍ ፖሊሲ ማመልከቻና ተጨማሪ መረጃ በሚከተለው ድህረ ገፅ ይገኛል http://www.inova.org/patient-and-visitor-information/financial-help/index.jsp፡፡

ማመልከቻው የገቢ ማሳያ እንዲሁም ስለ አንዳንድ ንብረቶች የሚገልፅ መረጃ (የጡረታ ሂሳብ መጠን፣ የባንክ ሂሳብ መጠን፣ አመልካቹ መኖሪያ ቦታውን የግል ወይም የኪራይ መሆኑ)፡፡ ግለሰቦች ማመልከቻውን መሙላት እና የተሞላውን ቅፅ ከሚፈለጉ ሰነዶች ጋር በማያያዝ ለሚከተልው አድራሻ ማስገባት አለባቸው፡

Inova Patient Financial Services<br>8095 Innovation Park Drive, Suite 501<br>Fairfax, VA 22031

በማመልከቻ ሂደት ላይ ድጋፍ ለማግኘት ፋይናንሳዊ ድጋፍ ክፍል በ 571-423-5880 በመደወል ያግኙ፡፡

የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻዎች በተቻለ ፍጥነት መግባት አለባቸው፣ ከዚያም የመጀመሪያው ከአገልግሎት በኋላ የሚሰጥ የሂሳብ መጠየቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ እስከ 240 ቀን ድረስ ማስገባት ይቻላል፡፡ የተሟላ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ከመጀመሪያው የክፍያ መጠየቂያ ቀን ጀምሮ 240 ቀናት በፊት ከገባ፣ Inova የብቁነት ምርመራውን በ FAP መሰረት ያካሂዳል፣ ለአመልካቹም ለየትኛው የድጋፍ አይነት ብቁ እንደሆነ በፅሁፍ ያሳውቃል፡፡ ያልተሟላ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ከገባ፣ Inova ማመልከቻውን ለማሟላት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን እና ሰነዶችን የሚገልፅ መረጃ በፅሁፍ ያቅርባል፡፡

የፋይናንስ ድጋፍ ውሳኔዎች አገልግሎቱ ብቁ ከሆነበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስተኛው(6ኛ)ወር የመጨረሻ ቀን ተቀባይት አለው፡፡ በዚህ የስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ፣ ታካሚዎች እንደገና እንዲያመለክቱ አይጠበቅባቸውም፤ ነገር ግን ተኝተው ለመታከም የሚመጡ ታካሚዎች ብቁ ሊሆኑባቸው ይችላሉ ተብለው ለሚታሰቡ በመንግስት የሚደገፉ ወይም የሚደጎሙ የጤና መድህን አገልግሎቶች በድጋሚ እንዲያመለክቱ ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡

የፋይናንሳዊ ድጋፍ ማመልከቻው ተቀባይነት ከሌለው ብቁ የሆነው አገልግሎት በቀረበበት ተከታታይ ግዜ ውስጥ የፋይናንሳዊ ድጋፍ አስፈላጊነት ይገመገማል፡፡

የInova እሴቶች የሆኑት የሰው ልጅ ክብር እና የአደራ ጠባቂነት መንፈስ በማመልከቻው ሂደት፣ በገንዘብ ድጋፍ ፍላጎት ምርመራ ሂደት እና በገንዘብ እርዳታው ጊዜ ሁሉ የሚንፀባረቁ ይሆናል፡፡ የገንዘብ ድጋፍ ጥያቄዎች በፍጥነት የሚስተናገድ ሲሆን፣ Inovaም የፍላጎት ምርመራውን ውጤት የተሟላ ማመልከቻ በተቀበለ በ 30 ቀናት ውስጥ የብቁነት ምርመራውን ውጤት ለማሳወቅ ኃላፊነት የተሞላበት ጥረት የሚደረግ ይሆናል፡፡

የ Inova ፋይናንሳዊ ድጋፍ ለማግኘት አመልካቾች የተጠየቁትን መረጃ ግዜውን ጠብቀው ማቅረብ፣ መንግስት ስፖንሰር የሚያደርጋቸው ወይ መንግስት የሚደጉማቸውን የጤና ኢንሹራንሶች ወይ ሌሎች ብቁ ለሚሆኑባቸው ፕሮግራሞች ላይ ማመልከትና እንዲሁም በታካሚውና በ Inova መካከል የሚደረጉትን የክፍያ እቅድ መሰረት የሚገባቸውን የክፍያ መጠን መክፈል አለባቸው፡፡

**የገንዘብ ድጋፍ ከሚፈልጉት ግለሰቦች ውጭ የሚገኙ መረጃዎች አጠቃቀም**

ብቁነትን በመለየቱ ሂደት፣ Inova የገንዘብ ድጋፍ ከሚፈልጉት ግለሰቦች ውጭ የሚገኙ መረጃዎችን ሊጠቀም ይችላል፡፡ ይህ፣ ከሚከተሉት አይነት ሲስተሞች የሚገኝ ዳታን ይጨምራል፡

- Inova የገንዘብ ድጋፍ ሊያስፈልጋቸው የሚችሉ ግለሰቦችን መለየት እንዲችል እና የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻውን እዲወስዱ የሚነገራቸውን ሰዎች ለመለየት የሚረዱን ሲስተሞች፤

- Inova በማመልከቻው ውስጥ በግለሰቦች የተሰጡ መረጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን ማረጋገጥ እንዲችል የሚያስችሉ ሲስተሞች፤
- Inova አንዳንድ መድህን የላቸውም ተብለው የሚታመኑ አካላት ቀድመው የሜዲኬድ ወይም ሌላ ሶስተኛ ወገን ብቁነት ያገኙ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችሉት ሲስተሞች፤ እና/ወይም
- ቀድሞ Inova ለገንዘብ ድጋፍ ያላቸውን ብቁነት ለመመርመር ሊቀበላቸው የሚችሉ የገቢ ወይም ሌላ ሰነዶች ስላሏቸው፣ ታካሚዎች፣ግለሰቦች የሴፍቲኔት ድርጅቶች (ለምሳሌ፡ በ ፌደራል ብቁ የጤና ማእከል) መሆናቸውን ለመለየት፡፡

**ክፍያ በማይፈፀምበት ግዜ የሚፈፀመው ሂደት**

በዚህ ፖሊሲ ስር ለፋይናንሳዊ ድጋፍ ያላመለከቱ ታካሚዎች የተለመደውን የ Inova ክፍያ አከፋፈልና አሰባሰብ ስር ይሆናሉ፡፡

በፌደራል መመርያዎች መሰረት ውጤታማ የክፍያ ሂደት ለማካሄድ ሁሉም የ Inova ሂሳብ የታካሚ ክፍል ግዴታዎች በ Inova ሂሳብ እና የመቀበል ስርዓት ይፈጸማሉ፡፡ የታካሚ ኃላፊነት የክፍያ ድርሻዎች ከክፍያ መጠየቂያ በፊት፣ በግለጫ እና ክትትል ሂደቶች ውስጥ ራስ ሰር በሆኑ አሰራሮች ውስጥ ያልፋሉ፡፡ ሁሉም የስብሰባ ርምጃዎች በፍትሃዊ የዕዳ አሰባሰብ ደንብ እና ACA ኢንተርናሽናል የስነምግባር መርኅ እና ሙያዊ ሃላፊነት መመሪያዎች መሰረት ይከናወናሉ፡፡

ታካሚዎች መግለጫዎችን ለ 120 ቀናት ያህል ይቀበላሉ፡፡ ከ 120 ቀናት በኋላ፣ ከታካሚው ምንም አይነት መልስ ካልተገኘ፣ እና ያንን የሚፈቅድ የአከፋፈል ስምምነት ከሌለ፣ ሂሳቡ ወደ ፕሮፌሽናል የዕዳ ሰብሳቢ ኤጀንሲ ይዛወራል፡፡ ዕዳ ከተጠቀሰው ጊዜ በላይ ከቀጠለ Inova በሂሳቡ ላይ ተጨማሪ ተግባራት ሊወስድ ይችላል፡፡

ታካሚው ክፍያ ለመፈፀም ማመቻቸት ከፈለገና ሒሳቡን ሙሉ በሙሉ መክፈል ካልቻለ ታካሚው ስላለው ሁኔታ ለ Inova ማሳወቅ እና Inova የክፍያ እቅድ ያቀርባል፡፡

ማንኛውንም የInova አካል ወይም የሶስተኛ-ወገን ተቀባይ ኤጀንት እንደ መጀመርያ ታካሚው በዚህ ፖሊሲ ስር ለፋይናንስ ድጋፍ ለመወሰን አሳማኝ ጥረት ሳያደርግ እንደ ህጋዊ እርምጃ ወይ በማንኛውንም ተቃራኒ የታካሚ ክሬዲት ተቃራኒ ሪፖርት ማድረግ ያሉ ልዩ የእርምጃዎች ስብብ *(Extraordinary Collections Actions) (“ECAs”))* አይጭንም፡፡ እነዚህ ምክንያታዊ ጥረቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

- ከመጀመርያው የሒሳብ መግለጫ ጀምሮ ቢያንስ ለ120 ቀናት ECA እንደማይጣል ማረጋገጥ፡፡
- ስለ Inova ፋይናንሳዊ ድጋፍ ፖሊሲና ክፍያ በማይፈፀምበት ግዜ ሊጣል ስለታሰበው ECA መረጃ ያካተተ የ30 ቀናት ማስታወቅያ ማቅረብ፡፡
- ክፍያ ባልተፈፀመበት ግዜ የታሰበውን ECA የቃል ማሳሰብያ መስጠት፡፡
- ታካሚው ክፍያ ከከፈለ በኋላ ወይ ECA ከተወሰነ በኋላ ፋይናንሳዊ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ መሆኑ ከተወሰነ ሒሳቡ ይስተካከላል እንዲሁም የአሰባሰብ አተገባበሩ ይስተካከላል፡፡
- የገቢ ሂደት ኦፐሬሽን ምክትል ፕሬዝዳንት ወይ ተወካዩ Inova ግለሰቡ ለFAP ብቁ መሆኑን ለማረጋገጥና አንድና ከዛ በላይ ECA መጣል እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው ለመወሰን ተገቢውን ጥረት እንዳደረገ ይከታተላሉ፡፡

## VI. ከፖሊሲው ጋር የተያያዙ መልእክቶች

**Inova ይህን ፖሊሲ በስፋት የሚያስተዋውቀው እንዴት ነው?**

Inova፣ ከእያንዳንዱ የ Inova አካል ጋር በመተባበር፣ የሚከተሉትን መንገዶች ተጠሞ ይህን የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ በስፋት ያስተዋውቃል፡፡

- Inova የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ እንዲሁም በድረ ገጹ ውስጥ ያለው FAP ግልጽ የቋንቋ ማጠቃልያ ወደ ፋይናንስ ድጋፍ ፖሊሲ *(Financial Assistance Policy (FAP))* እና ለእያንዳንዱ ሆስፒታል እና የታቀፈ ክፍል ይልካል፤

- የዚህ ፖሊሲ የወረቀት ቅጅዎች፣ የገዘብ ድጋፉ ማመልከቻ እና/ወይም የቀላል ቋንቋ ጨመቁ፣ በጥያቄ፣ በሕዝባዊ አካባቢዎች እና በፖስታ ያለክፍያ ይሰጣል፤
- የFAP የቀላል ቋንቋ ጨመቅ፣ የማስገባት ወይም የማስወጣት ሂደቱ አካል ሆኖ ይሰጣል፣ ይህም ታካሚዎች፣ መድህን የሌላቸውን ጨምሮ፣ በቂ መድህን የሌላቸው ወይም ራሳቸው የሚከፍሉ ሆነው የተመደቡትስለ ፖሊሲው መረጃ ያገኛሉ፤
- FAP, የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ፣ እና የ FAPው የቀላል ቋንቋ ጨመቅ ለብዙ ነዋሪዎች ይተረጎማል (ከ1000 ግለሰቦች ወይም በእያንዳንዱ የInova ሆስፒታል ወይም ተቋም ከሚገለገሉ ውስጥ 5 ፐርሰንት የሚያንሰው) እና የተገደበ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ላላቸው ሰዎች ይተረጎማል፤
- የክፍያ መጠየቂያዎች እና የመቀበያ ቅፆች ሁኔታዎች FAPውን በተመለከተ ግልፅ የሆኑ የፅሁፍ መልዕክቶችን ይይዛሉ (ስለ ገንዘብ ድጋፍ መረጃ መስጠት የሚችል የ Inova ክፍል ስልክ ቁጥርን ጨምሮ)፤
- ለአገልግሎት ክፍያ መክፈል ያለመቻል አዝማሚያ ለሚታይባቸው ሰዎች ሰዎች የቃል እና የፅሁፍ ማብራሪያዎች ይሰጣሉ፤
- Inova የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው ግልፅ በሆኑ የህዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች፣ አደባባዮች፣ እንዲሁም የድንገተኛ ክፍሎችን እና የታካሚዎች መመዝገቢያ ቦታዎችን ጨምሮ በእያንዳንዱ የ Inova ሆስፒታል፣ ተቋም እና የተሸፈኑ አካላት ሁሉ እንዲታይ ይደረጋል፤
- Inova የገንዘብ ድጋፍ የመፈለግ እድላቸው ከፍታኛ ከሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎችን የሚያገልግሉ የማኅበረሰብ ተኮር ድርጅቶች (ለምሳሌ በፌዴራል የታወቁ የጤማ ማ'ዕከላት እና ሌሎች የሴፍቲኔት ክሊኒኮች) የግልፅ ቋንቋ ጨመቁን ቅጅዎች ይሰጣል፣ እና
- ስለዚህ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ የሚገልፁ መረጃዎች፣ በማስታወቂያዎች እና በማኅበረሰብ ጥቅማጥቅሞች ማሳወቂያዎች ውስጥ በመደበኛነት እንዲካተቱ ይደረጋል፡፡

## VII. የተጨማሪ ህግጋቶች መረጃ

***በአጠቃላይ የሚጠየቅ ክፍያ (Amounts Generally Billed (AGB))***

የ Inova Health System ለፋይናንሳዊ ድጋፍ ብቁ የሆኑ ሰዎች አጠቃላይ ከሚከፍሉት መጠን በላይ እንዳይከፍሉ ያደርጋል፡፡ የ Inova Health System በፋይናንሳዊ ድጋፍ ስር የሚቀርበው ዝቅተኛውን ቅናሽ በውስጣዊ የገቢ ሕግ ክፍል 501(r) ውስጥ በተጠቀሰው ‹‹ሉክ ባክ›› (ወደ ኋላ ተመልከት) የሚለውን ዘዴ ይጠቀማል፡፡ ከዚህ ዘዴ ስር፣ ለ FAP-ብቁ ለሆኑ ግለሰቦች መቅረብ ያለበት ዝቅተኛው ቅናሽ ለእያንዳንዱ Inova Health System ሆስፒታል ተቋማትና በሚከተሉት አካላት የሚሰላ ነው፡

- Inova Health System ሉክ ባክ ዘዴን በመጠቀም አጠቃላይ የሚከፈለው መጠን *(Amount Generally Billed (AGB))* ይወስናል፡፡
- ለእያንዳንዱ የInova ሆስፒታል አገልግሎቶች AGB የሚሰላ ሲሆን የተሰላው የ AGB ቅናሽ በስርዓቱ ላይ የሚተገበር ይሆናል፡፡
- AGB አሊጋ ይዘው ለሚታከሙና ተመላላሽ አገልግሎቶች በግል ክፍያ ኢንሹራንስና (ሜዲኬርHMO ጨምሮ) ሜዲኬር (ባህላዊና የአገልግሎት ክፍያ) በሚጠየቀው መሰረት የሚሰላ ነው፡፡ በስሌቱ ውስጥ የማይከተቱ ከፋዮች ሜዲኬድ፣ በሂደት ላይ ያለ ሜዲኬድ፣ የበጓ አድራጎትና የግል ክፍያ ናቸው፡፡
- የ AGB ስሌት ለFAP-ብቁ ለሆነ ግለሰብ እንዲከፍለው እሚጠየቀውን ከፍተኛው ድምር የክፍያ ፐርሰንቴጅ ውጤት ነው (በግልባጩ የሚቀርበው ዝቅተኛው ፋይናንሳዊ ድጋፍ ቅናሽ)፡፡
- ዲሰምበር 31 የ12 ወራት የአመቱ ማጠናቀቅያ ከመድረሱ አስቀድሞ በእያንዳንዱ ዓመት በአፕሪል 1 AGB መሰራት አለበት፡፡ በ AGB ስሌት ላይ ማንኛውም ለውጥ ከተደረገ ይህ ለውጥ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በ120 ቀናት ውስጥ መተግበር ይኖርበታል፡፡

ስለ AGB እና ስሌት (ከክፍያ ነፃ ለሆኑ አገልግሎቶች) የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎትን በ571-423-5880 የInova ፋይናንሳዊ ድጋፍ ክፍል ያግኙ፡፡

**የደንብና ህግ ግዴታዎች**

ይህን ፖሊሲ በመተግበሩ ሂደት፣ ሁሉም የ Inova ሆስፒታል ተቋማት፣ የተሸፈኑ አካላት እና የተሸፈኑ አቅራቢዎች ከሁሉም ሌሎች የስቴት እና አካባቢያዊ ህጎች፣ ደንቦች እና ገዥ ስምምነቶች፣ እንዲሁም ይህን ፖሊሲ በማስፈፀም ሂደት ውስጥ የሚፈጸሙ እንቅስቃሴዎች ላይ ተፈፃሚነት ካላቸውን ደንቦች ጋር የሚስማማ ይሆናል፡፡